HYA



የአመራርነት መገለጫ/LEADERSHIP PROFILE ሪፖርት

የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools)

ሜይ/ጁን (May/June) 2026

HYA Corporation
909 W. Euclid Ave #926, Arlington Heights, IL 60006
Tel 847.250.7261

HYASEARCH.COM

ተጠቃሎ-የቀረበ ሪፖርት/EXECUTIVE SUMMARY

ይህ ሪፖርት፣ በጁን (June) 2026 ውስጥ፣ ለአሌክሳድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ ተተኪ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅን ለማግኘት፣ በ'Hazard, Young, Attea & Associates (HYA)' ተካሂዶ-የነበረውን፣ የአመራርነት መገለጫ ግምገማ (Leadership Profile Assessment) ላይ ያለውን ግኝት - የሚያቀርብ ነው። እዚህ የሚገኘው የመረጃ-ስብስብ/data የተገኘው፣ የHYA ኮንሰልታንቶች - ከግለሰቦች እና ቡድኖች ጋር - በየየግል ቃለ-መጠይቆች ወይም-ደግሞ በፎከስ ግሩፕ/focus group አቀማመጦች ላይ በተገናኙበት-ጊዜ ካገኙት አስተያየት፣ እና በባለድርሻ-አባላቶች/stakeholders ከተጠናቀቀው - ከአንላይን የዳሰሳ-ጥናት ውጤቶች - የተገኙ-ነበሩ። የዳሰሳ-ጥናቶቹ፣ ቃለ-መጠይቆቹ፣ እና የፎከስ ግሩፕ/focus group ስብሰባዎች፤ ቦርዱ - በአዲሱ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ ላይ የሚፈለጉትን ዋና-ዋና ባህሪያቶችን ለመወሰን-እንዲረዳው፣ አስተያየቶችን ለመሰብሰብ - የተዋቀረ-ነበር። በተጨማሪነትም፣ የባለድርሻ-አባላት/stakeholder ቃለ-መጠይቆች እና የፎከስ ግሩፕስ/focus groups - ስለ ዲስትሪክቱ ጠንካራ-ጎኖች እና በመጪው-ዓመታት ውስጥ የሚያጋጥመውን አንዳንድ አስቸጋሪና-ፈታኝ ነገሮች በተመለከተ - መረጃዎችን ሰብስቧል።

ተሳትፎ/PARTICIPATION

የተሳታፊዎች ቁጥሮች፣ በባለድርሻ-አባላት ቡድን/stakeholder group፣ በሁለት የመረጃ-ስብስብ/data የመሰብሰቢያ ዘዴዎች - ከዚህ-በታች ተዘርዝረዋል: *ሁሉም የፎከስ ግሩፕስ (focus groups)፣ ለአንላይን የዳሰሳ-ጥናት በምድብ-የተከፋፈለ - ቡድን አልነበሩም።*

ቡድን/Group	የየግል ቃለ-መጠይቆች ወይም 'focus groups'	የአንላይን የዳሰሳ-ጥናት
ቦርድ/Board	9	
በህንፃ ደረጃ ያሉ አስተዳደሮች	32	37
ሲኒየር አመራሮች & የማዕከላዊ ቢሮ አስተዳደሮች	39	
ተቋም/Faculty	7	134
ማህበረሰብ & ወላጆች	113	
ወላጆች/አሳዳጊዎች		392
የማህበረሰብ/የንግድ (Business) አባላቶች		64
እርዳታ-ሰጪ ሠራተኛ (Support Staff)	12	46
ተማሪዎች	32	86
የከተማ አስተዳደር	7	
አጠቃላይ/Total	251	759

የማህበረሰብ የዳሰሳ-ጥናት ሪፖርት እና የሚፈለገው ባህሪያቶች ረቂቅ፤ በተለያየ የሽፋን-ገጽ የቀረበ እና ለአመራርነት መገለጫ ሪፖርቱ (Leadership Profile Report)፣ በእያንዳንዳቸው ለየብቻ የተዘጋጁ ሆነው - ሲጣመሩ-ግን ሚዛናዊ-አመለካከትን የሚሰጡ ሆነው-የቀረቡ ናቸው።

የመረጃ-ስብስቡ/data - ሣይንሳዊ የናሙና-አቀራረብ አለመሆናቸውን - ወይም-ደግሞ በየተለያየ ቡድኖች/respective groups ለቀረቡት አብዛኛዎቹን አስተያየቶች የሚወክሉ-ሆነው መታየት የሌለባቸው መሆኑ፣ አጽንዖት ሊሰጥበት የሚገባው ጉዳይ ነው። በኮንሰላታንቶቹ/consultants ዕይታ፣ የቦርዱን ትኩረት የሚሹ ሆነው ከተገኙ፣ ጉዳዮቹ/Items - ተካተዋል።

የዲስትሪክቱ ጠንካራ-ጎኖች

የአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (The Alexandria City Public Schools (ACPS)፣ የተለያየ-ስብጥር ያለው የተማሪ አካል እና ማህበረሰባቸውን በሚደግፍ - መሠረታዊ-የሆነ ጠንካራ-ጎኖቹ፣ ተለይተው ይታወቃሉ። ቀደምት-የሆነው ጠንካራ-ጎኑ - የዲስትሪክት ስብጥሩ/district's diversity ሲሆን፣ ይህም ሰፊ፣ በዓለም-አቀፍ ደረጃ የተቀላቀሉ ተማሪዎችን፣ ቤተሰቦችን፣ እና ሠራተኞችን - ከ127 በላይ ቋንቋዎችን በአንድ-ላይ የሚያመጣ እና የተለያዩ-ዓይነት ባህላዊ ተሞክሮዎችን - ወደ መማሪያ አካባቢው በማምጣት - ያለውን-ማንነቱ ይገለፃል። ይህ - የተማሪዎችን የአካዳሚክ እና ማህበራዊ-ስሜታዊ ሁኔታዎች ላይ ተማሪዎች የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ለማሟላት - አብዛኛውን-ጊዜ ከሚፈለገው-በላይ በመሄድ-በሚሰሩት፤ በጠንካራ እና ከፍተኛ ቁርጠኝነት-ያላቸው ሆነው-በሚገለጹት - ትጉህ እና ተሰጥዖ-ያላቸው ትምህርት-ሰጪ ሠራተኞች እና አስተዳደሮች፣ የተጠናከረ-ነው።

ዲስትሪክቱ በተጨማሪም፤ ተማሪዎቹን - ሁሉን-አቀፍ በሆነ የአካዳሚክ የመጓጓ-መንገዶች/academic pathways፣ እንደ - የከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት አካዳሚስ ሞዴል/Academies model፣ ጥምረት-ያለው ምዝገባ (dual enrollment)፣ እና የስራ-መስክ ላይ ትኩረት ያደረገ ሰርቲፊኬት-አሰጣጥ ባለው ውስጥ፣ ይህም - ከሁለተኛ-ደረጃ በኋላ (post-secondary) ላለው-ዝግጅት፣ ጉልህ-በሆነ ሁኔታ ወደሚያግዛቸው - እርዳታ-ይሰጣል። እነዚህ ጥረቶች፤ ስኮላርሽፖች/scholarshipsን፣ ኢንተርንሽፖች/internshipsን፣ እና ወሳኝ-ሆነው የሚያስፈልጉ የመረጃ-ምንጮችን ለማግኘት - የተስፋፋ ዕድልን ከ140 በላይ ከሆኑ መደበኛ ትብብር-አድራጊዎች ጋር በመሆን፣ በጠንካራ ማህበረሰብ እና ካለ-ትርፍ የሚሰሩ አጋርነቶች/non-profit partnerships አማካኝነት ተጠናክሮ-የሚከናወኑ ናቸው። በተጨማሪነትም፤ የዲስትሪክቱ ስትራቴጂካዊ ጂኦግራፊያዊ-አቀማመጥ፣ በዋሽንግተን ዲሲ (Washington, D.C.) አቅራቢያ ለሚገኙ - ተማሪዎችና ሠራተኞች ልዩ የባህል ተቋሞችን እና በጣም ርቀው በሚገኙ የትምህርት ቤቶች ዲስትሪክቶች ውስጥ በቀላሉ የማይገኙ የሙያ ልምዶችን - እንዲገኙ በማድረግ፣ ያቀርባል።

ጥልቅ-ትኩረቱን - በማህበራዊ-ስሜታዊነት (social-emotional) ትምህርት፣ ሁሉን-በማካተት/inclusion፣ እና እንደ ዓለም-አቀፍ አካዳሚ (International Academy) ባሉ ስርዓቶች ውስጥ እርዳታን-አስተካክሎ በማስቀመጥ፣ ተማሪን-ማዕከል ባደረገ/student-centered የእርዳታ-አሰጣጥ ላይ ያለው ቁርጠኝነት - የክፍል-አቀፍ/division-wide ቀደምትነት-የሚሰጠው ነው። ይህ - በከፍተኛ-ደረጃ የማህበረሰብ ተሳትፎ የተደገፈ ነው፤ ይህም - የጋለ-ስሜት ያላቸው ባለድርሻ-አባላቶች/stakeholders - በዲስትሪክቱ ስኬት ላይ - ጥልቅ-በሆነ ሁኔታ ኢንቬስት አድርገው-በመቆየታቸው ነው። ከዚህም-በተጨማሪ፣ ባለድርሻ-አባላቶች/stakeholders - መካከለኛ-መጠን ያለው ክፍል/division ቅልጥፍና -

እንደ ቁልፍ-የሆኑ ጠንካራ-ጎን አድርጎ በተደጋጋሚነት የሚጠቅሱት ሲሆን፣ ይህም - ግላዊ-የሆነ የእርስ-በርስ ግንኙነቶች፣ በሠራተኞች መካከል ቤተሰብ-መሠል አቀራረብን እና አዳዲስ ተነሳሽነቶችን በፍጥነት የመተግበር አቅም - እንዲኖር ያስችላል።

በመጨረሻም፤ ጠንከር-ያለ የስነ-ጥበባት/arts እና ከትምህርት-በኋላ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች (extracurricular activities) ውስጥ፣ ተማሪዎች - እንደ 'band'፣ 'choir'፣ 'theater'፣ 'robotics'፣ እና 'JROTC' ባሉት-ነገሮች ዙሪያ፣ ለመሳተፍ የሚያስችላቸውን ዕድሎች - ACPS ያቀርባል። እነዚህም፣ በጠንካራ መሠረታዊ-በሆነ እና የቅድመ ልጅነት ትምህርት (early childhood education) በመደገፍ-የሚቀርቡ ናቸው፤ ይህንንም - ባለድርሻአባላቶች/stakeholders - የመጀመሪያ-ደረጃ ተማሪዎችን፣ ወደ መካከለኛ/middle እና ከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት - ጠንከር-ወዳለው የአካዳሚክ ትምህርት በተሳካ-ሁኔታ ለማዘጋጀት፣ ወሳኝ-መሆኑን አጽንዖት ሰጥተዋል።

ዲስትሪክቱ እየገጠመው-ያለው አስቸጋሪና-ፈታኝ ነገሮች እና ጉዳዮች

የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፣ እየጨመረ-ባለው የሰው-ኃይል ወጪዎች/labor costs፣ የአዲሱ የጋራ ስምምነት አተገባበር ውስብስብነት፣ እና ውስን-ዓመታዊ የገንዘብ ድጋፍ መጨመርን - አካትቶ፣ ጉልህ-የሆኑ የፋይናንሺያል መሰናክሎችን ይጋፈጣል። ከእነዚህ የበጀት-ግደባዎች ጋር ተጨማሪ-በመሆንም፣ ዕድሜአቸው-እየጨመረ የመጣው ተቋሞች - ከ80 ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው እና በተለይ በመካከለኛ-ደረጃ (middle) ትምህርት ቤት ደረጃ ስር-በሰደደ ሁኔታ ከመጠን-በላይ አጨናንቀው-በመያዛቸው፤ ያለውን የመሠረተ-ልማት ችግሮች አሳሳቢ አድርጎታል። ዲስትሪክቱ፤ ዕድገትን እና የስነ-ሕዝብ ለውጦችን - ከድርጅታዊ ቋሚ-ሆኖ የመቆየት አስፈላጊነት እና ወጥ-የሆነ/coherent፣ የረጅም ጊዜ ራዕይ - ከማስፈለጉ-ጋር፣ ሚዛኑን-ለመጠበቅም እየታገለ ነው።

ዲስትሪክቱ፤ እየቀጠለ-ያለውን የቀለም-ትምህርት ውጤታማነት ክፍተቶችን ለመዝጋት ቅድሚያ-ይሰጣል፤ ባለድርሻአባላቶች/stakeholders እንደአስተዋሉት - ሂሳብ/math እና ELA የክንውን-ሂደት የውጤት-ደረጃዎች፣ መጠነ-ሰፊ የመረጃ-ምንጮች/resources ቢኖሩትም እንኳን - እድገት እያሳዩ አይደሉም። ይህ የስራ-ተግባር/task፤ ውስብስብ-የሆኑ፣ ስብጥር-ያለውን የተማሪ አካልን - ለመደገፍ-በመቻል ላይ፤ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የእንግሊዘኛ ቋንቋን የሚማሩ/English Learner (EL) እና ኢሚግራንት ተማሪዎች - የሚያስፈልጋቸውን በቀውስ-ላይ መረጃ-ያለው እንክብካቤ-አሰጣጥን እና አብዛኛውን-ጊዜ አሁን ባለው የሠራተኛ-አመዳደብ ደረጃዎች - በደንብ-እርዳታ ሊሰጥባቸው ያልቻለውን - በልዩ-ሁኔታ የሚፈለጉ የመረጃ-ምንጮች (specialized resources)ን በማቅረብ ላይ፣ አስቸጋሪና-ፈታኝ ሁኔታዎችን ያካተተ-ነው። በተጨማሪነትም፤ የደህንነት-ጥበቃ ስጋቶች—ከማንጓጠጥ/bullying እና የጋንግ ተጽዕኖ/gang influence ጀምሮ - እስከ የካምፓስ የጥበቃ-ሁኔታ/campus security—ለመማሪያ አካባቢው - በተለይ-ደግሞ በከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት ደረጃ-ላይ ለሚገኙ፣ እንደ ትልቅ እንቅፋት ተደጋግመው የሚጠቀሱ ናቸው።

የዲስትሪክቱ/district - ወሳኝ-የሆነው ጉዳይ፣ እምነትን ወደነበረበት መመለስ እና በማህበረሰቡ፣ በትምህርት ቤት ቦርድ፣ በከተማው ምክር-ቤት እና በከተማው ስራ-አስኪያጅ መካከል ያለውን ግንኙነቶች እንደገና የመገንባት አስፈላጊነት-ነው፣ ይህም-የሆነው - አንዳንዶች፣ ግልጽነት እና የግንኙነት-ማድረግ ጉድለቶችን - በመጥቀሳቸው ነው። እነዚህ አስቸጋሪና-ፈታኝ ነገሮች፤ በውስጣዊ-አሰራር ላይ ተንጸባርቀዋል፣ በማዕከላዊ ቢሮ እና በትምህርት ቤት-ደረጃ ላይ ባሉ ቡድኖች መካከል ያለው መረጃዎችን ሳያካፍሉ-ማቆየት/communication silos መኖሩን መገንዘብ፣ በብዙዎች ዘንድ ግልጽ-ያልሆነ እና ከላይ ወደ-ታች የሚታይ - ድርጅታዊ መዋቅር እንዲኖር አድርጓል። ከዚህም-በተጨማሪ፣ ሠራተኞን-በስራው ላይ ማቆየት/staff retention እና የሞራል/morale - ዝቅተኛ-ሆኖ የተወሰዱ ሲሆን፣ ይህም-የሆነበት ምክንያት - ተወዳዳሪነት-የሌለው የማካካሻ-ክፍያ፣ ከፍተኛ-የኑሮ ወጪዎች፣ የአመራርነት እርዳታ-ሰጪነት አለመኖር ሆኖ - ይህ ሁሉ፣ ክፍሉ/division -

ውስብስብ እና አብዛኛውን-ጊዜ አስቸጋሪና-ፈታኝ-የሆኑ የውጪ የፖለቲካዊ አቀራረቦች (external political dynamics)ን በመዳሰስ-እየመራ በሚገኝበት ጊዜ-ነው።

'HYA' እና 'ቦርዱ/the Board'፤ ክፍሉ/division የሚያስፈልጉትን ሁሉ ለማሟላት የሚያስችል አብዛኛዎቹን ችሎታዎች እና ባህሪያቶችን የያዘን ግለሰብ የመፈለግ - አስቸጋሪና-ፈታኝ የሆነውን ተግባር-ለማሟላት - ይሠራሉ። የፍለጋ ቡድኑ/The search team፤ ከACPS ቦርድ ጋር ለመስራት የሚችል - የእያንዳንዱ ትምህርት ቤቶች እና ማህበረሰቦች ልዩ-ሆነው የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች እያሟላ-በመስራት፣ የአካዳሚክ ደረጃዎች/standardsን እና የተማሪ የክንውን-ሂደትን ከፍ-በማድረግ ለመቀጠል አስፈላጊ-የሆነውን አመራርነት ሊያቀርብ የሚችል - አዲስ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ (superintendent) ለማግኘት እየፈለገ ነው።

የፍለጋ ቡድኑ/The search team፤ በፎከስ ግሩፕስ/focus groups ስብሰባዎች የተሳተፉትን ወይም የኦንላይን የዳሰሳ-ጥናትን ላጠናቀቁት፣ እና በስብሰባዎቻችን እርዳታ-ላደረጉ የ'ACPS' የሠራተኛ-አባላቶች - በተለይ-ደግሞ ዶ/ር ጀምስ ዴተን (Dr. James Deaton) እና ታኒካ ቴለር ተካን (Taneika Taylor Tukan)ን - የፎከስ ግሩፕ/focus group የጊዜ-ደሌዳዎችን በማዘጋጀት ለተሳተፉት-ሁሉም እና የፍለጋ ቡድኑ/search team በዲስትሪክቱ ውስጥ ለነበረው ጊዜ፣ ምስጋናችንን-እናቀርባለን።

HYA | EDUCATION EXPERTS

ተፈላጊ-የሆነው - የተተኪ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ ባህሪያቶች
የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools)

ለዲስትሪክቱ የሚቀጥለው ትምህርታዊ መሪ ሆኖ - የሚያስፈልገውን ችሎታዎች እና ባህሪያቶች ለመለየት እንዲረዳ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ/Alexandria City School Board፤ ከተማሪዎች፣ ወላጆች፣ ሠራተኞች፣ እና የማህበረሰብ አባላቶች ጋር - በፎከስ ግሩፕስ/focus groups፣ በቃለ-መጠይቆች፣ የማህበረሰብ ፎረሞች እና በዲጂታል የአስተያየት መስጫ-ሂደት አማካኝነት - የአመለካከት-አስተያየትን ለማግኘት ይጠይቃል። በዚህ የአመለካከት-ሃሳብ ላይ መሠረት-አድርጎ፣ በበርካታ የባለድርሻ-አባል ቡድኖች/stakeholder groups በተገለጸው-መሠረት፣ ለአዲሱ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ ተፈላጊ-የሆኑ ባህሪያቶች፤ **ተማሪን-መጀመሪያ ባደረገ ሁሉን-አንድ በሚያደርግ ራዕይ፣ የስብጥር-ልዩነት ቁርጠኝነት-ባለው፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ እና ጥልቅ-የሆነ የከንውናዊ-ሂደት እና የፋይናሺያል የብቃት-ደረጃ ባለው** ዙሪያ ማዕከል-አድርጓል።

ዋና የባለሞያነት እና የአመራርነት ልዩ የላቀ-ብቃቶች/Core Professional & Leadership Qualities

- **ባለራዕይ & ስልታዊ/Visionary & Strategic:** ግልጽ፣ የረጅም-ጊዜ ራዕይ ያለው መሪ - የድርጅታዊ ቋሚነትን፣ ከፍተኛ የአካዳሚክ ደረጃዎች/standards ማቅረብ የሚችል እና ውስብስብ-የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት "አርቆ-ማሰርብ/think out-of-the-box" የሚችል።
- **ውሳኔ-ሰጪ እና ተጠያቂነት-ያለው/Decisive & Accountable:** አስቸጋሪ፣ በመረጃ-ስብስብ/data ላይ የተመሠረተ ውሳኔዎችን ለማድረግ ፈቃደኝነት ያለው፣ ለተገኙት ውጤቶች ባለቤትነትን-የሚወስድ፣ እና ተማሪው ለሚያገኘው-ውጤቶች ሁለቱንም-እራሳቸውን እና ሠራተኛውን - ተጠያቂ-እንዲሆን ማድረግ የሚችል - መሪ።
- **ልምድ እና ከዚህ-ቀደም ያከናወናቸውና የስኬት-ውጤቶች/Experience & Track Record:** ከፍተኛ ልምድ ላለው የጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ የከንውን-ስራ፣ ለተማሪ ውጤታማነት፣ ትልቅ፣ ውስብስብ እና የስብጥር-ልዩነት ያለውን የትምህርት ቤት ክፍሎች/divisions በማሻሻል ላይ - በደንብ-ከተረጋገጠ ከዚህ-ቀደም ያከናወናቸውና የስኬት ውጤትን ያስመዘገበ፣ እና ስኬታማ-የሆነ የአስተዳደር ለውጥን በማስፈጸም-ያከናወነ።
- **የከንውናዊ-አሰራር እና በፋይናሺያል-ነገሮች ላይ ፈጣንና-ትክክለኛ ውሴን-አሰጣጥ/Operational & Financial Acumen:** ጠንካራ-የሆነ የአስተዳደራዊ ችሎታዎችን የያዘ፣ የበጀት ትንበያን-በሚገባ የሚገነዘብ፣ ከንውናዊ-ሂደትን ወደ የላቀ-ደረጃ የሚመራ፣ እና የመማሪያ-ክፍል የትምህርት-አሰጣጥን በአሉታዊ-ሁኔታ ተጽዕኖ ሳያደርግበት - የብቃት-ቅልጥፍናዎችን መለየት-የሚችል።

የአመራርነት ስልት እና ራዕይ/Leadership Style & Vision

- **መገኘቱ-የሚታይ እና ተሳታፊ-መሆን/Visible and Engaged:** በትምህርት ቤቶች ውስጥ በአካል-መገኘት የሚችል፣ ለሠራተኞች እና ተማሪዎች በቀላሉ-መገኘት-የሚችል እና የጋራ እምነት እና ክብር ያለውን-አካባቢ ለማደራጀት የሚችል - መሪ።
- **አዎንታዊ-ለውጦችን የሚያደርግ እና ውሳኔ-ሰጪ/Transformational and Decisive:** አስቸጋሪ-የሆኑ ውሳኔዎችን ለማስፈጸም የማይፈራ፣ እንደ-ለውጥ አምጪ-ሆኖ የሚያገለግል፣ እና ክፍሉ/divisionን ለማሻሻል - ሊመጡ-የሚችሉትን አደጋዎች ቀድሞ-በማስላት እርምጃ-ለመውሰድ ፈቃደኛ-የሆነ።
- **ቁርጠኛ-የሆነ እና ለረጅም-ጊዜ አገልግሎት-የሚሰጥ/Committed and Long-term:** ይህን የስራ-ሚና እንደ - በስራ-መስክ ውስጥ ወደሌላ-መሸጋገሪያነት መጠቀሚያ ሳይሆን እንደ የረጅም-ጊዜ ቁርጠኝነት አድርጎ-የሚመለከት፣ እና ከማህበረሰቡ ጋር አንድ-የተዋሃደ ክፍል ለመሆን ፍላጎት-ያለው።
- **አልበገር-ባይ እና በቀላሉ-የማይረበሽ/Resilient and Thick-skinned:** የዲስትሪክቱን ውስብስብ-የሆኑ ፖሊሲዎችን መርምሮ-መፈተሽ የሚችል እና ልዩ-የሆኑ ፍላጎት-ያላቸውን ቡድኖች - በዲስትሪክቱ ተልዕኮ ላይ ያለውን-ትኩረት ሳያጣ - ማሰማት የሚችል፣ መሪ።

ግንኙነቶች-የሚፈጥር እና እምነትን መገንባት/Relationship & Trust Building

- **የመሸጋገሪያ-ድልድይ ገንቢ-የሆነ/Bridge Builder:** የጋራ-የሆነ ግንኙነቶችን - ከትምህርት ቤት ቦርድ/School Board. የከተማ ምክር-ቤት/City Council፣ የከተማ አስተዳደር/City Manager እና ከማህበረሰቡ ጋር - ለመገንባት ወሳኝ-ሆኖ የሚያስፈልግ መስፈርት።
- **የሌሎችን-ሁኔታ በመገንዘብ - የሚያዳምጥ/Empathetic Communicator:** በንቃት የሚያዳምጥ፣ ግልጽነት-ያለው፣ እና ከስብጥራዊ-ልዩነት ካላቸው ቡድኖች ጋር በቅልጥፍና-ግንኙነት በማድረግ፣ እንግሊዘኛ-ቋንቋ ቀደምት-የሆነ ቋንቋቸው ያልሆኑትን ጨምሮ - መሳተፍ-የሚችል መሪ።
- **ተባባሪ/Collaborative:** የአስተማሪዎች፣ የእርዳታ-ሰጪ ሠራተኞች (support staff) እና የወላጆችን የአስተያየት-ሃሳቦችን አግኝቶ ለመረዳት እና ዋጋቸው-ትልቅ እንደሆነ የሚያውቅ፣ ፊት-ለፊት መስመር-ላይ ባሉት አገልግሎት-ሰጪዎች ውሳኔዎች - መረጃ-እንዲያገኙ ሆኖ-መሰጠቱን የሚያረጋግጥ - መሪ።

በቀለም-ትምህርት ላይ ያተኮረ & ተጠያቂነት (Academic Focus & Accountability)

- **ተማሪን-ማዕከል ያደረገ/Student-Centered:** በምንም-ነገር የማይናወጥ ትኩረትን - በሁሉም ተማሪዎች በትምህርታዊ-ሂደት ላይ በሚያስፈልጓቸው ነገሮች ላይ የሚያደርግ፣ የተማሪን ውጤቶች እና የመማር ተሞክሮአቸውን - ከውስጣዊ ፖለቲካ ወይም ለሌላው-አስመስሎ ከማቅረብ (politics or optics) አስበልጦ - ቀደምትነትን የሚሰጥ።

- **ውጤቶችን-ለማምጣት ያተኮረ/Results-Oriented:** በምንም-ነገር የማይናወጥ ትኩረትን - የአካዳሚክ ውጤቶች/Academic Outcomes (math/ELA scores)ን በማሻሻል ላይ የሚያደርግ፣ የውጤታማነት ክፍተቶች/achievement gapsን መዝጋት፣ እና የከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት የአካዳሚክስ ሞዴል/academies modelን በአሌክሳንድሪያ ባለ-ብዙ ካምፓስ (multi-campus) ከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚገኙ ሁሉም ተማሪዎች - ማጠናከር።
- **በመረጃ-ስብስብ የተደገፈ/Data-Driven:** የመረጃ-ስብስብ/dataን በመጠቀም - መረጃ-ያለውን የውሳኔ-አሰጣጦችን በማድረግ የሚወስነው - የትምህርት-አሰጣጥ መሪ፣ ለክንውን-ሂደቱ - ክፍሉ/divisionን ተጠያቂ-አድርጎ የሚይዝ እና ለሁሉም ተቀጣሪ-ሠራተኞች በከፍተኛ-ሁኔታ የሚጠበቁባቸውን ደረጃዎች-ያስቀምጣል።
- **ልምድ ያለው/Experienced:** ተመጣጣኝ-በሆነ፣ የስብጥር-ልዩነት ባለው እና ውስብስብ-በሆነ - የከተማ ትምህርት ቤቶች ክፍሎች/divisions ውስጥ፣ በስኬት-በመስራት ላይ ቀድሞ-ያስመዘገባቸው የስኬት-ውጤቶች ያለው - ብቃቱ-የተረጋገጠለት መሪ።

የክንውናዊ-አሰራር፣ ፋይናንሺያል & የተሰጥዖ ፈጣንና-ትክክለኛ ውሴን-አሰጣጥ/Operational, Financial & Talent Acumen

- **አካላዊ ኃላፊነት/Fiscally Responsible:** ፈጠራዊ-የሆነ የበጀት-አጠባበቅ፣ ውሱን-የሆኑ የመገኛ-ምንጮችን/resources በአግባቡ መቆጣጠርን፣ እና ለአካባቢ፣ ስቴት፣ በፌደራል-ደረጃዎች ላይ ያሉ የገንዘብ-እርዳታን ለማግኘት ተሟጋች-የመሆን አቅም-ያለው መሪ።
- **በክንውናዊ-አሰራር ብቃት-ደረጃ/Operationally Competent:** የክንውናዊ-ሂደት የላቀ-ደረጃ (operational excellence) ያለውን ጠቃሚነት-የሚገነዘብ—እንደ - የተቋም ጥገና/facility maintenance፣ መጓጓዣ/transportation፣ እና የደህንነት-ጥበቃ/safetyን—እነዚህ ለስኬታማ የመማሪያ አካባቢ - መሠረታዊ-ነገሮች መሆናቸውን እውቅና-የሚሰጥ።
- **ተሰጥዖ-ያለውን ማግኘት እና በቅጥር-ላይ ማቆየት//Talent Acquisition and Retention:** የተማሪውን አካል እና ማህበረሰቡን የሚያንጸባርቅ፣ የስብጥር-ልዩነት ያለውን ተሰጥዖ-ያላቸውን ለመመልመል እና በቅጥር-ለማቆየት - ያለውን የብቃት-አቅም ያሳየ። የረጅም-ጊዜ ግቦችን ከውሱን-የሆኑ የመረጃ-ምንጮች ጋር፣ የተቋሙን እና የሠራተኛውን የብቃት-አቅም ለመገንባት እንዲረዳ፣ ፈጠራዊ-የሆነ የምልመላ ስልቶችን የማስፈጸም አቅም-ያለው።

ባህላዊ የብቃት-ደረጃ እና ሁሉን-አካታችነት/Cultural Competence & Inclusivity

- **ፍትሃዊ-እኩልነት ላይ ትኩረት ያደረገ/Equity-Focused:** የዲስትሪክቱን የስብጥር-ልዩነት ላይ እውን-በሆኑ መንገዶች ዋጋ-የሚሰጥ፣ የስደተኛ ቤተሰቦችን እና የእንግሊዝኛ ቋንቋን ለሚማሩ (English Learners) ልዩ-ሆነው የሚያስፈልጓቸውን-ነገሮች የሚገነዘብ እና ፍትሃዊ-እኩልነት የመረጃ-ምንጭ/equitable resourceን ማከፋፈልን ላይ የሚያበረታታ - መሪ።
- **ባህላዊ የብቃት-ደረጃ/Culturally Competent:** ለዲስትሪኩት ዓለም-አቀፋዊ ማህበረሰብ (127+ ቋንቋዎች) ላለው - አክብሮት-ያለው እና ሁሉን-የሚያካትት አካባቢን በመንከባከብ-ለማሳደግ ቁርጠኝነት ያለው - መሪ።

የአመራርነት ልምዶችን እና ውጤታማነቶችን በተመለከተ፣ ተተኪ-የሆነው የACPS ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ እጩ - የሚከተሉት ያሉት-ይሆናል:

- ተመሳሳይ-የሆነ ጠንካራ-ጎኖች፣ ውስብስብነት፣ ስነ-ሕዝብ ብዛት/demographics እና አስቸጋሪና-ፈታኝ ሁኔታዎች ባለው ማህበረሰብ ውስጥ፣ ከፍተኛ-የሆነ ስኬታማ ትምህርታዊ እና የትምህርት-አሰጣጥ አመራርነትን - ያሳየ።
- ለ‘Virginia DOE 8 VAC 20 - የክፍሉ የጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ ፈቃድ/Division Superintendent license’ ያለው ወይም ወዲያውኑ ብቁነት-ያለው።

የማካካሻ-ክፍያ/Compensation:
ለበርካታ-ዓመታት ኮንትራት የሚሰጥ - ወደ $305,000 ከሚደርስ ደሞዝ ጋር - በእውን-ካለው የብቁነት-አቅም፣ ልምድ፣ የማስረጃ-ምስክሮች/credentials እና የድርድር-ውይይቶች/negotiations ጋር - ሊለወጥ የሚችል። ከሌሎች የዲስትሪክት ተቀጣሪ-ሠራተኞች ጋር ተመሳሳይ-የሆነ፣ ለ‘VA statues’ ተግባራዊ-የሚሆን እና በድርድር-ውይይት/negotiation ሊለወጥ-የሚችል - ጥቅማ-ጥቅሞች/Benefits።

ፍላጎት-ያላቸው እና ብቁነት-ያላቸው ግለሰቦች፣ ስለዚህ ክፍት-የስራ ቦታ - በዚህ ላይ በመጫን፣ የበለጠ ለማወቅ እና ለማመልከት ይችላሉ:
https://hyasearch.com/job/superintendent-alexandria-va/